# መጽሐፍ ቅዱስ ለህፃናት
## አቅራቢዎች

# ኢየሱስ ታላቁ መምህር



ጸሐፊው: Edward Hughes
ምሣሌ አቅራቢው: Byron Unger; Lazarus
ያሻሽለው (አሻሽሎ የጻፈው): E. Frischbutter; Sarah S.
የተተረጎመው: Eyerusalem Dechasa
Alastair Paterson
አዘጋጁ: Bible for Children
www.M1914.org

BFC
PO Box 3
Winnipeg, MB R3C 2G1
Canada

©2020 Bible for Children, Inc.
**ፈቃድ**፡- ይህንን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ማባዛት ወይም ማተም ይቻላል



ኢየሱስ
ታላቁ እና
ምርጡ
መምህር ነው። ብዙ ሰዎች
ኢየሱስን
አዳምጠውታል። ኢየሱስም መሐሪ, ጥሩ እና
ደግ እንዲሆኑ ይነግራቸው ነበር። ሌሎቹ



ኢየሱስ ብዙ
ነገሮችን ለህዝቡ
ያስተምር ነበር።
የእግዚአብሔር
ህዝቦች ሻማ ቤትን
በሚያበራበትን
መንገድ ለአለም
ማብራት
እንዳለባቸው
ያስተምራቸው
ነበር። ሻማ
በጨለማ ክፍል
ውስጥ ያለው
ልዩነትንም
አስረዳቸው።

ኢየሱስም ለህዝቦቹ "ዓይን ስለ ዓይን,
ጥርስ ስለ ጥርስ" ብሎ ስለበቀል
አስተማራቸው። ሆኖም ግን ኢየሱስ
ለጠላቶቹ እንኳ
ደግነትን፣ ይቅርታን እና
ፍቅርን አስተማረ።





በኢየሱስ ዘመን አንዳንድ ሰዎች ራሳቸውን በጣም ቅዱስ እንደሆኑ አድርገው ያቀርቡ ነበር። ለለማኞች ገንዘብ ሲሰጡ አንድ ሰው መለከት እንዲነፋ ያደርጉ ነበር በዚህም ሁሉም ሰው እንዲያያቸው ያደርጉ ነበር። ኢየሱስም "የምትሰጡትን ስጦታ በድብቅ አድርጉ እግዚአብሔርም ይከፍላችኋል" አላቸው።

ኢየሱስ ስለ ጸሎት ተመሳሳይ ነገር አስተማረ። አንዳንድ ሰዎች በጎዳናዎች ማቆሚያ ስፍራዎች ይጸልያሉ ስለዚህ ሁሉም ሰው ያያቸዋል፣ ይሰማቸዋል። ስለ እግዚአብሔርም ግድ የላቸውም። ግድ የሚላቸው ሰዎች ስለነርሱ የሚያስቡት ነገር ነበር። ኢየሱስም እነርሱን ሂፖክራይት በማለት ሰየማቸው። ትርጓሜውም ሀሰተኛ ተዋናዮች ማለት ነው።



ኢየሱስ ብዙውን ጊዜ ለትምህርቶቹ ተፈጥሮን እንደምሳሌ ተጠቅሟል። ለምሳሌ, ወፎቹን ጠቅሷል። "የሰማዩ አባታችው ይመግባቸዋል" ብሏል። "አትጨነቁ ለእናንተም እንዲሁ እግዚአብሔር ይመግባችኋል።"



ኢየሱስ "ባለፀጋው ንጉሥ ሰሎሞን እንኳን እንደ አበቦች የደመቀ ልብስ አልለበሰም" በማለት ቀጠለ። "እግዚአብሔር ሜዳን በሣር ካለበሰ እናንተን እንዴት አያለብሳችሁም?" ኢየሱስ ለሰዎች የሚያስፈልጋቸውን ሁሉ የሚያቀርብላቸውን እግዚአብሔርን እንዲታመኑ ያስተምራቸው ነበር።



"በወንድምህ
የምትፈርድ ከሆነ
ይህ ማለት
በዓይኖችህ ውስጥ
ትልቅ ምሰሶ እያለ
የወንድምህን ትንሿን
ጉድፍ ለማውጣት
መሞከር ማለት
ነው። ምናልባት
ሰዎች ያሾፉበት
ይሆናል። ነገር ግን
ትርጉሙን መፈለግ
ነበረባቸው።





ኢየሱስም ሰዎች
የእግዚአብሔርን
እርዳታ መጠየቅ
እንዳለባቸው ተናገረ።
ምድራዊ አባት
የተራበ ልጁ ዳቦ
ሲጠይቀው ድንጋይ
ይሰጠዋል? አይ!
መልካም ነገር
ይሰጠዋል እንጂ።
እግዚአብሔርም
እንዲሁ ለሚለምኑት
መልካም ነገሮችን
ይሰጣቸዋል።

ታላቁ አስተማሪ ኢየሱስ ስለ ሐሰተኛ አስተማሪዎች አስጠነቀቀ። ኢየሱስ "የበግ ለምድ ይለብሳሉ ውስጣቸው ግን ተኩላዎች ናቸው" በማለት ተናገረ። ሐሰተኛ መምህራን በሚኖሩት ህይወት እንደሚታወቁም ተናገረ።



በታሪኩ ውስጥ ኢየሱስ የእግዚአብሔርን ቃል የሚታዘዙ ሰዎች ቤቱን በዓለት ላይ የሠራን ሰው እንደሚመስሉ አሳያቸው።



ኃይለኛ አውሎ ነፋስ ተነሳ ነገር ግን ቤቱ ጸንቶ ቆመ።

ሰነፍ ሰው ግን ቤቱን በአሸዋ ላይ ሠራ። ዐውሎ ነፋሱም መጣ ደካማ መሠረት በመሆኑ ምክንያት ፈራረሰ። ኢየሱስም የእግዚአብሔርን ቃል የማይታዘዙ እንደዚህ ሰው ናቸው ብሎ ተናገረ።



ሕዝቡም ኢየሱስ በተናገረው ነገር
እጅግ ተደነቁ። ከዚህ በፊት እንዲህ
ያለ ነገር ሰምተው አያውቁም ነበር።
አሁን የእግዚአብሔርን ቃል ለማወቅ
ይህ ብቻ በቂ እንዳልሆነ አወቁ።
በየቀኑ መታዘዝ ይኖርባቸዋል።



# ኢየሱስ ታላቁ መምህር

ይህ ታሪክ የሚገኘው የእግዚአብሔር ቃል
በሆነው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ

ማቴዎስ 5-7፤ ሉቃስ 6

“የቃልህ ፍቺ ያበራል.”
መዝሙረ ዳዊት 119:130

# መጨረሻ

42

60

ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ የሚያስተምረን ግሩም ስለሆነው አምላካችን እግዚአብሔር እኛን በመፍጠሩ እሱን እንድታውቀው ነው።

እግዚአብሔር “ኃጢአት” ብሎ የሚጠራውን ክፉ ነገር እንዳደረግን ያውቀዋል። የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነው ነገር ግን እግዚአብሔር በጣም ስለወደደን አንዱንና ብቸኛው ልጁን ለቀራኒዮ መስቀል ሞት አሣልፎ በመሥጠት እንዲሞትና የኃጢአታችንን ዋጋ በእኛ ምትክ በመሞት እንዲከፍል አደረገው። ኢየሱስ ከሞት ከተነሣ በኋላ በምድር ላይ ቆይቶ ወደ ሠማይ ወደ አባቱ አረገ! ያላመንን እኛም በኢየሱስ አዳኝት ብናምን እና ኃጢአታችንን ይቅር እንዲል ብለምነው ይቅር ይለናል። ደግሞም ያደርገዋል። እሱም በእኛ ውስጥ ይኖራል፤ እኛም በእርሱ ውስጥ ለዘላለም እንኖራለን አሜን።

ይህ እውነት እንደሆነ ካመናችሁ፣ እግዚአብሔርን እንዲህ በሉት ጌታ ኢየሱስ ሆይ አንተ አምላክ እንደሆንክ አምናለሁ ነገር ግን ለእኔ ኃጢአት ለመሞት ስትል ሰው ሆንህ አሁን ደግሞ ህያው ነህ። እባክህ ወደ ህይወቴ ግባ ኃጢአቴን ይቅር በል በዚህም አዲስ ህይወት አሁን ይኖረኛል አንድ ቀን ከአንተ ጋር ለዘልዓለም ለመኖር ወደ አንተ እመጣለሁ። ለአንተ እንድኖርና እንደ ልጅ እንድታዘዝልህ እርዳኝ። አሜን።